# የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስለመውሰድ ግዴታ ማብራሪያ

## የኖርዌጅኛ ቋንቋ እና የህብረተሰብ ትምህርት ስለመማር ግዴታ

በኖርዌይ ለመኖር ፈቃድ ካገኙ የሚከተሉት መብቶች ለመጠየቅ ዕድል ይሰጥዎታል፣
♦ቀዋሚ የነዋሪነት ፈቃድ እና/ወይም
♦የዜግነት መብት ።

የቀዋሚ ነዋሪነት ፈቃድ ወይም የዜግነት መብት ለማግኘት ከሚያስችሉ ነገሮች መካከል 300ሰዓታት ማለትም፥
♦የኖርዌጅኛ ቋንቋ ትምህርት /250 ሰዓታት/ እና
♦የህብረተሰብ ትምህርት / 50ሰዓታት /የመፈፀም ግዴታ ይኖርብዎታል ።

ይህ የስልጠና ግዴታ ግን ምዝገባ ወቅት ዕድሜዎ 55 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

ለስልጠናው ወጪም ራስዎ መክፈል ይጠበቅብዎታል።

ከስልጠና ግዴታው ነፃ ለመሆን ማመልከት የሚችሉት፥
♦የኖርዌጅኛ ወይም ሳሚኛ ቋንቋ በቂ ችሎታ ያልዎት መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ወይም
♦በተለይ ደግሞ የጤና እክል ወይም ሌላ አሳማኝ ምክንያት ካለዎት ይሆናል።

**ተጨባጭ መረጃ**
ስልጠናውን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ መረጃ ከፈለጉ በተመዘገቡበት የህዝብ ምዝገባ ፅህፈት ቤት አቅራቢያ በሚገኘው የማዘጋጃ ቤቱ /ኮሚኒ / የማሰልጠኛ ማእከል ዘንድ በአካል ቀርበው ማመልከት ይችላሉ። የምዝገባ ቀን ማጠናቀቂያ ለማወቅ ወይም መብትዎን
በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ወይም መረጃ ከፈለጉ ከማሰልጠኛ ማእከሉ ጋር መገናኘት ይችላሉ።
ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ከሚከተሉት ድረገፆች ማግኘት ይችላሉ።

www.imdi.no እና
www.udi.no